# *ብፁዕ አቡነ ፈሪሳዊ፣ አቡነ ቢሽፍቱ ወአባ በከንቱ!*

ያለንበት ዘመን ጳጳስት ሳይቀሩ የሸፈቱበትና የድንግርግር ዘመን በመሆኑ ብዙ ሕዝብ ተደናግሯል። ክህነት ወይም ሌዋዊነት ምን ማለት ነው? ለዋዊ ወይም ካህን ማን ነው? ሌዋውያን ወይም ካህናት ምን ይሠራሉ? በማለት ብዙዎቻችን ለመጠየቅ ተገደናል፣ ጥርጣሬ ውስጥም ገብተናል። ስለዚህ ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ *ብፁዕ አቡነ ፈሪሳዊ፣ አቡነ ቢሽፍቱ ወአባ በከንቱ* በሚል ርዕስ እንሆ መልስ ትጽፏል።

፩ኛ. <<*ተክህነ -አገለገለ*>> ከሚል ግስ የወረደ ቃል፣ በጥንታዊው ኢትዮጵያዊኛው ቋንቋችን ከግዕዝ የተገኘ፣ ከኦሪት ጀምሮ ደብተራ ኦሪት፡- …ቅድስተ-ቅዱሳኒቱን ሲያገለግሉ የነበሩት ሌዋውያን ይጠሩበት የነበረ፣ የመንፈሳዊያን ልዩ መጠሪያና መዓርግ ነው። በዚህ መሠረት ካህን ማለት አገልጋይ ወይም ሌዋዊ ማለት ነው። ካህናት ሕዝበ-እግዚአብሔርና ቤተ እግዚአብሔርን ያገለግላሉ፤ በንጽህናቸው፣ በብቃታቸው እግዚአብሔር መርጧቸዋል፤ እና፣ …ዐዕይነተ እግዚአብሔር፣ ሰላማውያን ወይም መልከጼዴቃውያን ተብለው ይጠራሉ፤ እንደ መላእክት ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ እያሉ ሌትና ቀን እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ።

፪ኛ. በቅኔ ቤት የቃላት ግሳዊ አወራረድ፣ አተረጓጎም እና አፈታት <<*ሌወወ -ጠመጠመ*>> ማለት ከሊቃውንት ጥምጥም ወይም የሊቅነት መለያ እና የክብር አክሊል ጋር ይዛመዳል። ነገር ግን ካህን ነኝ በማለት እንደ *እነአቡነ ቢሽፍቱና አባ በከንቱ* ትልቅ ቆብ የሰቀለ፣ መስቀሉን የጨበጠ እና የጠመጠመ ሁሉ ካህን ወይም ሌዋዊ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ፣ ስንዴውን ከእንክርዳዱ ማበጠርና …ማብጠርጠር ይገባናል።

፫ኛ. በሌዋዊነት ወይም በክህነት ሽፋን በሌብነት፣ በመጠራጠር፣ በክሕደት፣ በውርደት፣ በቅሌትና ዕብደት በተካኑት *በነአቡነ ፈሪሳዊ፣ አቡነ ቢሽፍቱ እና አባ በከንቱ* ግን <<*ሌወወ -ጠመጠመ*>> ማለት፣ ነገር መጠምጠም፣ ተንኮለኛ፣ ምሥጢረኛ፣ የተሸፋፈነ ጉዳ-ጉድ እና ጉድፍ ተሸካሚ፣ ክፉ፣ ትዕቢተኛ፣ ትምክሕተኛ፣ ጨካኝ፣ ደፋር፣ ዓይን-አውጣ፣ ወራዳ፣ ዘረኛ እና ብልጣ-ብልጥ ሆኖ መገኘት ነው ብለው ይፈቱታል። እንዲሁም የአጭበርባሪዎች እና የአባይ-ጠንቋይ ምልክት…ወዘተ. ተደርጎ ይተረጎማል። በዚህ ዓይነት መንፈሳዊ ሕይወትና ትርጉም የሌለው ኑሮ የሚኖሩ ሰዎችም ጥምጥሙን ይጠመጥሙታል። *እነአቡነ ፈሪሳዊ* በቆብና ጥምጥም ሽፋን ካህናት ነን፣ ሌዋውያን ነን ይላሉ። እነዚህ ሳያውቁ፣ ሳይበቁ፣ ሳይማሩ፣ ሳይመራመሩ፣ ትሕትና እና ፈሪሐ እግዚአብሔር ሳይኖራቸው፣ እውቀቱን ሳይጥሙ የጠመጠሙ አስመሳዮች ስለሆኑ፣ የክህነት እንክርዳድ እንጂ ካህናት ተብለው መጠራት አይገባቸውም። (Shame on them)

ትክክለኛው ሌዋዊነት (ክህነት) ሌዊ ከሚባል የመጀሚርያው አባት ስም ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። ሌዊ የመጀመሪያው ካህን ስለ ነበረም ክህነት ከቤተ ሌዊ አይወጣም ተብሎ የሌዊ ዘር በሙሉ ቤተ ሌዊ (ቤተ ክህነት) እየተባለ ይጠራ ነበር። በዚህ ምክንያት ኦሪታዊው ክህነት ማለት ሌዋዊነት ከቤተ ሌዊ አይወጣም ተብሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ በውርሻ ሲተላለፍ ነበር። በአገራችን፣ በኢትዮጵያም ዘር-መንዘራቸው ቤተ ክህነት እየተባሉ ሓረገ-ትውልድ የሚቆጠርላቸው ወገኖች አሉ።

አጀማመሩም፡- በምሳሌያዊ አነጋገር፣ <<*ከሰው መርጦ ለሹመት፣ ከዕንጨት መርጦ ለታቦት*>> እንዲሉ፣ ሌዋውያንን ለሌዋዊነት የመረጣቸው እና ለዚህ አገልግሎት የለያቸው እግዚአብሔር ነበረ እንጂ በገዛ ራሳቸው

የመረጡት ወይም በራሳቸው ፍላጎት የጀመሩት የአገልግሎት ክፍል አልነበረም። ከዚህ ማንኛውም ነገር ካለእግዚአብሔር ፈቃድ የማይሆን መሆኑን ማስተዋል እንችላለን። ሌዋውያን በነቢይ ሙሴ አቅራቢነት በእደ አሮን ተቀብተው ከእግዚአብሔር የተቀበሉት የአገልግሎት ክፍል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ነገደ ሌዊ ከተቀሩ ነገደ እስራኤል ተለይተው እግዚአብሔርን ለማገልገል በእግዚአብሔር ተመርጧል፤ (ዘኍልቍ፡ ም. ፫፥ ቍ. ፱-፲፬)። በተጠቀሰው ኃይለ ቃል መሠረት፣ ነገደ ሌዊ ከነገደ እስራኤል የነገድ ቍጥር ወጥተው፣ ነገደ እግዚአብሔር ሆኗል። በዚህ የመመረጥ ዕድል፣ ካህናት እግዚአብሔርን ለማገልገል ብቻ እንደተለዩ የእግዚአብሔር ቃል ነግሮናል፤ ትክክለኛው የሌዋውያን ምንነትና ትርጉም ይህ ነው።

ካህናት ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ግብረ-ክህነት ውጭ ሌላ ዓለማዊ ወይም ፖለቲካዊና የጥቅም ጉዳይ ከክህነታዊ ሥራ ጋር ቢቀላቅሉ ካለሥራቸው እንደገቡ ነው የሚታወቀው። መንፈሳዊውን ሥራ ከዓለማዊው ሥራ ጋር ሰለ ቀላቀሉም ራሳቸውን ለመርገም አሳልፈው እንደ ሰጡና ፈጠሪያቸው እግዚአብሔርን እዳስቀየሙ መታወቅ አለበት። ባልተመረጡበት ሥራ ላይ ቢሰማሩና ቅድስናቸውን ቢያራክሱ፣ መቅሰፍትና የእግዚአብሔር ቁጣ ወደ ዓለም እንደ ሚያስመጡብን በእግዚአብሔር ቃል ተነግሮናል፤ …ይቀጣሉ፣ ተቀጥተውም ያስቀጡናል። (ትንቢተ ሚልኪያስ፡- ም. ፪፥ ቍ. ፱-፲)። በዚህ ኃይለ-ቃል፣ *<<…እናንተ ግን ከመንፈሴ ፈቀቅ ብላችኋል፤ …የሌዊን ቃል ኪዳን አስነውራችኋል፤ …ስለዚህ መንገዴን እንዳልጠበቃችሁ፥ በሕግም ለሰው ፊት እንዳዳላችሁ መጠን፥ እኔ ደግሞ በሕዝብ ፊት የተናቃችሁ እና የተዋረዳችሁ አደርጋችኋለሁ>>* ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መሠረት ነቢዩ ሚልክያስ የተናገረው የእግዚአብሔር የቁጣ ቃል ነው። *እነአቡነ አቡነ ቢሸፍቱ* ግን ጥንቃቄ የጐደለባቸው፣ ቃሉን በመተላለፍ በሌብነት፣ በክሕደት፣ በቅሌት፣ በዕብደትና ውርደት ላይ የተሰማሩ ሆነው ተገኝቷል። ይህ ማስጠንቀቅያም በቀጥታ የዘመኑ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳትና መነኮሳት (ካህናት/ሌዋውያንን) የሚመለከት ነው።

ከእግዚአብሔር ቃል የላቀ መካሪ ሊገኝ አይችልም እና በቃሉ መሠረት፣ *እነአቡነ ቢሸፍቱ* ተመክረው በንስሐ ቢመለሱ ራሳቸውን ያድናሉ፣ እግዚአብሔርም ይደሳታል። ማስረጃውም፡- *<<ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል>>* ይላል የሉቃስ ወንጌል ም. ፲፭ ፥ ቍ. ፯። ይህ በትንቢት እና በምሳሌ መልኩ የተላለፈልን፣ እኛን ለማዳን፣ ለምክርና ለተግሳፅ የተፃፈልን የእግዚአብሔር ቃል ነው።

በተለይ በስመ መንፈሳዊነት እየተንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያንን በማፍረስ ላይ ያሉትን ለማስጠንቀቅ የተነገረ ጥብቅ አምላካዊ ቃል ነው። እነዚህ ቃሉን በመተላለፍ ካህናት በመምሰል እና *<<ሌወው፡ ጠመጠመ>>* የሚለውን ማደናገሪያ በመጠቀም ትላልቅ ቆብ ወይም ጥምጥም አድርገው፣ ቀሚስ አጥልቀው፣ መስቀሉን ጨብጠው፣ በደረት አንጠልጥለው ቤተ ክርስቲያንን በማፍረስ ተግባር ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በእርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ኢትዮጵያዊ ጨዋነት አስገድዶት አባቶቻችን እያለ ያከብራቸዋል። በአፍራሽ እና አስነዋሪ ሥራዎቻቸው ግን ያፍርባቸዋል፤ …ሁላችንም እናፍርባቸዋለን።

*እነአቡነ ቢሸፍቱ* ቤተ እግዚአብሔር እና ሕዝበ እግዚአብሔርን ለማገልገል የተሰጣቸውን ክህነትና የአብያተ ክርስቲያናት የስብከተ-ወንጌል መድረኮች ሁሉ እንደ ዋና የፖለቲካ መቀስቀሻ፣ የዘረኝነት ማጠናከሪያ፣ የጠብና ልዩነት ማስፋፊያ ይጠቀሙበታል። ወንጌልን እንሰብካለን በሚል ሽፋን፡- *እነአቡነ*

*ቢሸፍቱ* የጠሉትን ሲያወግዙ፣ ሲጠሉና ሲያጥላሉ፣ በዲያብሎስ እያስመሰሉ ሲስሉ፣ ሲያራክሱና ስም ሲያጠፉ ይታያሉ። *እነአቡነ ፈሪሳዊ፣ አቡነ ቢሸፍቱ እና አባ በከንቱ* አእምሮአቸው በፖለቲካ በመመረዙ በቀጥታ የፖለቲካ ተሳትፎ ለማድረግ በየፖለቲካ ድርጅቱ በሕቡዕ ወይም በግልፅ በመሳተፍ ሲጨማለቁ ይታያሉ። ሃይማኖትን እና ፖለቲካን በማዛባረቅ ካለቦታቸው ገብተው ሰውን ያስቀይማሉ፣ እግዚአብሔርም ያስቆጣሉ። ይህ የሌዋውያን ማለትም የካህናት ሥራ ሊሆን አይገባውም ብቻ ሳይሆን ያልተጠሩበት የሥራ ዓይነት በመሆኑ በትንቢቱ መሠረት በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስቀጣቸው ነው። ስለዚህ ይህ ዓይነቱ ክህነት ከሌብነት ከቅሌት፣ ከአጭበርባሪነት፣ ከዕበደትና ውረድት እንጂ ከሌዋዊነት ግንኙነት ሊኖረው አይችለም።

*እነአቡነ ቢሸፍቱ* በነቢየ እግዚአብሔር በሚልክያስ በተነገረን መሠረት በተቀብአ ያገኙትን እና እንዲገለገሉበት ሳይሆን እንዲያገለግሉበት በአደራ የተቀበሉትን ክህነት ከፖለቲካ ጋር ማዛባረቅ ማለት እንክርዳዱን ከንፁህ የሥንዴ መስዋዕት ጋር ቀላቅለው ለእግዚአብሔር ተቀባይነት የሌለው መስዋዕት እንዳቀረቡ ይቆጠራል። ይህ ንፅህና የጐደለው መስዋዕት እግዚአብሔር አይቀበለውም ብቻ ሳይሆን የሚያስቆጣው ነው። የእግዚአብሔር ቁጣም ደግሞ እንደ ቃኤል የሚያስረግማቸው፣ እንደ ናዳብና አብዩድም የሚያስቀስፋቸው ነው። በታሪክ ይወቀሳሉ፣ እኛም እናዝንባቸዋለን፣ እናፍርባቸዋለንም፤ ...(Shame on them)።

የእግዚአብሔር ቁጣ ለአሮን ልጆች፣ ለናዳብ እና ለአብዩድ አልጠቀማቸውም፤ በሲና ምድረ በዳ በእግዚአብሔር ፊት በድፍረት ልዩ እሳት *(ልዩ መስዋዕት)* ባቀረቡ ጊዜ በመቅሰፍት *ሞቱ*፣...የሞት ቅጣት ተቀጡ። የሰዉት መጥፎ መስዋዕት ባስከተለባቸው መርገም ሳቢያም ዘር አላስቀሩም፣ ፈጽመው ጠፉ፣ ይለናል፤ (ኦሪት ዘኍልቍ ም. ፫፥ቍ. ፬-፭)። በአሁኑ ዘመን በስመ ክህነት፡- በስመ በጵጵስና፣ በስመ ሊቀ ጵጵስና፣ በስመ ቁምስና በተለይ ክህነትን ከምንኵስና ጋራ በማገናኘት እና የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት *እነአቡነ ቢሸፍቱ* እግዚአብሔር የማይቀበለው መስዋዕት እና ቅዳሴ በእግዚአብሔር ፊት ያሳርጋሉ። ሌዋዊው ሓላፊነት (ክህነት) በማይገባ መልኩ ተገቢ ባልሆነ ቦታ ሁሉ ለዓለማዊ-ሥጋዊ ጥቅም መጠቀሚያ ይገለገሉበታል። በሃይማኖት ሽፋን ሕዝቡን መጠቀሚያ ለማድረግ በዓለማዊ ፖለቲካዊ ዘይቤ፣ በከፋፍለህ ግዛ፣ ቤተ ክርስቲያችን ከፋፍሏታል። ሰይጣን ባጠመደብን መንገድ፡- በጎሣ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ የአቡነ እገሌ፣ የአባ እገሌ፣ የአቶ እገሌና የዶ/ር እገሌ በማለት በየፊናችን ከፋፍለውናል። በዚህም እናፍርባቸዋለን።

ከሁሉም በላይ በከፋ መልኩ ሊገለፅ የሚችል በደል አድርሰውብናል። እሱም፡- *እነአቡነ ቢሸፍቱ* የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በአስተዳደር እንድትከፋፈል በውጭ ሀገር ሕጋዊ ያልሆነው ሲኖዶስ በማቋቋማቸው ነው። ይህ ታሪካችንን የሚያበላሽ እና በሚቀጥለው ትውልድም የሚያስወቅስ ታላቅ በደል መሆኑ ነው። ይህ በደል ደግሞ በመንፈሳዊያን ነን ባዮች አባቶች፡- በጳጳስት፣ በኤጲስ ቆጶሳት፣ በካህናት/በሌዋውያን መደረጉ ደግሞ ይበልጥ አሳዛኝ ያደርገዋል። *እነአቡነ ቢሸፍቱ* ራሳቸውን በገዛ-ራሳቸው እንደሚያንቆላጵሱት፣ መንፈሳዊያን አባቶች ከሆኑ፣ ስለሰላም፣ ስለፍቅር፣ ስለይቅርታ፣ ስለኅብረት፣ ስለአንድነት እና ክርስትያናዊ መልካም ነገር ማስተማርና መስበክ በተገባቸው ነበር እንጂ እንዴት ጳጳሳት እርስ በራሳቸው ተጣልተው ይለያያሉ? እነዚህ አባቶች በዓለመ ነፍስ እና በዓለመ ሥጋ በሁለቱም በኩል የተጐዱ በኪሳራ ላይ ኪሳራ ተደራርቦባቸው የከሰሩ ነጋዴዎች ናቸው፤ ያሳፍራሉ!! *(Shame on them)*።

፩ኛ. እነ*አቡነ ቢሸፍቱ* እና እነ*አባ በከንቱ* ዓለመ ሥጋ ሁሉ እርኵስ ነው፤ መንፈስ እና ዓለመ ነፍስ ግን ንጹህ ነው በሚል ነፍስን እና ሥጋን የሚያጣላ አመለካከት እና አጉል ፍልስፍና በመከተል፣ ዓለሙን ሳይጠላቸው ጠሉት። እንድያውም ይህ እኛ ምድራውያን መላእክት ነን፤ ንጹሃን፣ ብፁአን፣ ቅዱሳን እና ብቁዎች ነን የሚያሰኛቸው ትምክሕት፣ ትዕቢት እና አባዜ ያስከተለባቸው ውድቀት ሳይሆን አይቀርም። በዓለመ ሥጋ በይፋ ወልደው፣ ከብደው እና ዘምደው፣ ወደው እና ተወደው፣ እንደ ዓለማውያን በዓለሙ እንዳይደሰቱ፣ ራሳቸውን ከዓለሙ ምለው፣ ተገዝተው፣ ሙተውም ተገንዘው ተለይቷል። ከዓለም ሙተናል፣ ከሥጋዊ ነገር ተለይተናል ብሏል። ነገር ግን ወደ ዓለሙ በጓዳው እንደ ሌባ በኋለኛው በር ሾልኰው በመግባት በፖለቲካው፣ በጥቅምና በመሳሰለው ዓለማዊ ጉድፍ ሲጨማለቁ ይታያሉ። ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው የሚሸሽ፣ ይቅርታን የማያውቁ፣ በቂም-በቀል የተካኑ፣ በሥልጣን የሚባልጉ፣ ዘረኞች፣ ወገንተኞች፣ ጐጠኞች፣ ጠባቦች እና ትምክሕተኞች ሆነው ተገኝቷል። *(Shame on them)*

፪ኛ. በመንፈሳዊ ዓለም እንዳይጠቀሙ ደግሞ እንዲሁ ኢክርስቲያናዊ ሥራ በመስራት እንደ ናዳብ እና እንደ አብዩድ ሰውን እና እግዚአብሔርን ያስቀይማሉ። ስለዚህ እነዚህ አባቶቻችን ያልታደሉ፣ በሁሉም የተጐዱ ናቸው። በጣም ያሳዝናሉ፣ ከዚህ ዓለም በማይቀርላቸው ዕዳ፣ በሞት በሚያልፉበት ጊዜም በራሳቸው ታሪክ (Legacy) ላይ ጥለዉት የሚያልፉት ጠባሳ ወይም መጥፎ ታሪክ እንኳ ማየት አልቻሉም። ስለዚህ ቅዱስ ዳዊት፣ «*ዓይን በሙ ወኢይሬእዩ፣ እዝን በሙ ወኢይሰምዑ*» እንዳለው (Shame on them) እንዞ እነ*አቡነ ቢሸፍቱ* በቂም-በቀል፣ በዘረኝነት፣ በጠባብነትና ...በትምክህት ዕዉራነ ልብ ሆኖዋል ማለት ነው።

ከኢትዮጵያ ውጭ ለሲኖዶስ ማቋቋም ሊሰጠው የሚገባ ትርጉም፣ ዕብደት ነው። አንድነቷ ለዘመናት ተጠብቆ፣ ተከብራ እና ታፍራ ትኖር የነበረችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አምጣ የወለደቻቸው፣ ያሳደገቻቸው፣ አስተምራ ያከበረቻቸው የገዛልጆቿ ጳጳሳት፣ እነ*አቡነ ቢሸፍቱ* ወገቧ ላይ ሲቆርጧት፣ የውስጥና የውጭ በማለት ሲከፋፍሏት ከማየት የከፋ እሳዛኝ ነገር ሊኖር አይችልም። በውጭ አገር በስደት የሚገኝ ሕዝባችን ሲኖዶስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አያውቀውም በሚል አመለካከትና ንቀት ሊሆን ይችላል፣ ሲኖዶስ አቋቍመንልሃል፤ በኢትዮጵያ ሕጋዊ ሲኖዶስ የለም፤ ሲኖዶስ (ሃይማኖት) ተሰዷል፤ ...ወዘተ...ወዘተ. በማለት አማኙን ሕዝብ ግራ-ቀኝ እያዋከቡ ያታልሉታል።

ሲኖዶስ ማለት ምን ማለት ነው? በኢትዮጵያ ሲኖዶስ ማለት መንፈሳዊ መንግሥት ማለት ነው። ይህ ማለትም ለብሔራዊትዋ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ቁንጮዋ እና የበላይ ጠባቂዋ ሲኖዶሱ ነው ማለት ነው። ስለዚህ የዚህች ቤተ ክርስቲያን ተከታይ የሆነው ሕዝብ እምነቱን እና አንድነቱን ጠብቆ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ማለት ነው። እንደ ሲኖዶሱ ገንጣዮች፣ እንደ እነ*አባ ቢሸፍቱ* ከተረጎምነው ግን ሲኖዶስ ተሰዷል ብሎ ማውራት ማለት አገሩቱ፣ *ኢትዮጵያ* ተሰዳለች ብሎ እንደ ማውራት ማለት ነው። እነሱ ስለተሰደዱ ደግሞ በኢትዮጵያ ሰው አልቀረም ማለታቸው ነው። ስለዚህ በስደት ሲኖዶስ ማቋቋም ማለት በሰማዩ ደመና ላይ በሕልም እና በቅዠት፣ ሥእል ሠርቶ ሌላ ኢትዮጵያን እንደ መፍጠር ማለት ነው። እንደ ጤነኛ ባለአእምሮ በሚያስብ ሰው ደግሞ ይህ የሚታሰብ አይደለም። ስለዚህ ከኢትዮጵያ ውጭ ሲኖዶስ ማቋቋም ማለት ትርጉሙ ከአእምሮ ውጭ መዋለል፣ ቅዠት እና ዕብደት ነው።

ይህንን የመሰለ ዕብደትና ውርደት ተሸክመው የሚዞሩ ሰዎች ካህናት/ሌዋውያን ተብለው ሊጠሩ አይገባቸውም። እናት ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከውርደት እና ከዕብደት በንስሐ እንዲመለሱ ጊዜ ስጥታና መክራ አንመለስም ካሏት በኋላ በአደራ የሰጠቻቸው መዓርገ-ክህነቱን መልሳ መውሰዷ ይታወሳል። ስለዚህ እነዚህ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሕግና ሥርዓት ውጭ የሚሰውት መስዋዕት እንደ መስዋዕተ ቃኤል፣ እንደ መስዋዕተ ናዳብና አብዩድ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያጣ እና ያልተቀደሰ መስዋዕት ነው። ከእናት ቤተ ክርስቲያን ውጭ አፈንግጠው የሚቀድሱትና የሚሰዉት ስለሆነም መስዋዕታቸው መስዋዕተ ቃኤል ነው እንጂ መስዋዕተ አቤል ሊሆን አይችልም፤ ጐደሎ ነው፣ ቅድስናም የለውም። ጳጳሳት እና መነኮሳት ሲሸፍቱ፣ ሲሰደዱ፣ ሲሳደቡ እና በየሆቴሉ አስረሽ-ምች ሲሊ የታዩበት ታሪክና ጊዜ የለም። ይህ ከሕግ ውጭ ብቻም አይደለም፣ ፍፁም ውምብድና እና ኢክርስቲያናዊ ሥራ ነው።

ስለዚህ እነዚህ ሰዎች የሚቀድሱትን ቅዳሴ ለመስማትና የሚሰዉትን መስዋዕት ለመቍረብ (ለመቀበል) የሚኼዱ ሰዎች የክሕደት፣ የዕብደት፣ የውግዘት፣ የመረገም እና የመለየት ተባባሪዎች መሆናቸው ነው። ይህም እራስን በራስ እንደማውገዝ፣ መለየትና መገዘት ይቆጠራል። በመሠረቱ ሰውን እና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት የዕርቅ መስቀል ለይስሙላ ካህናት …መንፈሳዊያን አባቶች ለመምሰል እና ለጌጥ በእጅ ይዘውት፣ በደረት አንጠልጥለውት ይታያሉ፤ የመስቀሉ ሥራ ግን አይሠሩም። የእነ*አቡነ ቢሸፍቱ* ቅዳሴ ማሳረጊያውን ልብ ብላችሁ ከስተዋላችሁት ደግሞ እርግማን እና ልቅሶ ነው። ሕዝቡን እንደ ደንቡ «*በሰላም ወደ የቤታችሁ ግቡ*» ብለው ሳይሆን የሚያሰናብቱት እግሌ ጠላታችሁ ነው፤ ከእነ እገሌ ጋር እንዳትተባበሩ የሚል ነው። ይህ ከካህናት ከመንፋሳዊያን አባቶች አይጠበቅም። በዚህ መሠረት ሌቦች፣ ወንበዴዎችና ‹*ካህናት ነበር*› (Ex-communicated) ተብለው በነበር ነው መጠራት ያለባቸው።

ጥምጥሙን ያሳመረ፣ መስቀል የጨበጠ፣ ቆብ የሰቀለ እና ቀሚስ ወይም ልብሰ-ተክህኖ ያጠለቀ ሁሉ ካህን ሊሆን አይችልም። ለነገሩማ ይሁዳም እኮ ሐዋርያ ነበር …እና እንጠንቀቅበት እንጂ ጐበዝ! ትክክለኞች ሌዋውያን /የእግዚአብሔር ካህናት በሥራቸው ይለያሉ፡- የተጣላውን ወገን ያስታርቃሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል ይሰብካሉ፣ መጥፎ ነገር እና ስድብ አይወጣባቸውም፣ ይቅር ባዮች ናቸው፤ ፖለቲካ ውስጥ አይገቡም፣ ከቂም-በቀል እና ከመሳሰለው መጥፎ ነገር ይርቃሉ እንጂ ጠብና ረብሻ ወዳለበት ዞር አይሉም። ሰለዚህ ሰላማውያን ወይም መልከ ጼዴቃውያን ካህናት ተብለው በሥራቸው ይለያሉ፤ …እነዚህን እንከተል።

ከዚህ ውጭ የሆኑት ደግሞ አንጻራዊ ወይም ሰይጣናዊ ሥራ ይሠራሉ፡- መስቀሉን እንደዱላ እያወጣወጡ ወደ አምባ-ጓሮ፣ ሀውከትና ብጥብጥ ወዳለበት ቦታ ሁሉ ይገሰግሳሉ፤ ዘረኝነት፥ ትምክሕተኝነት እና ጠባብነትን በመሸፋፈን ቃለ እግዚአብሔር አስመስለው በቀደሱባት ቤተ መቅደስ መግቢያ ላይ ሆነው መርዛቸውን ይረጫሉ። እነአ*ቡነ ቢሸፍቱ!* አጭበርባሪዎች፣ ፈሪሳውያን፣ ጸሐፍት፣ ሰዱቃውያን እና አማሌቃውያን ናቸው፤ …እነዚህን አውቆ-አጥፊዎች ማወቅና መራቅ እንጂ እነሱን መከተል አይገባም።